# በከሰሩ ፖለቲከኞችና አክራሪዎች ጋብቻ የሚቀፈቀፉ

# ሽብርተችና መዘዛቸው (፩)

## አብዱልአዚዝ    08/05/13

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት "ሽብርተኝነት እና የሃይማኖት አክራሪነት ስጋት መሆናቸውን እና እንዲሁም ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሃይማኖትን ጉዳይ የፖለቲካ ትርፍ እናገኝበታለን ብለው  በማሠብ እየተጠቀሙበት  መሆኑን አዲስ አበባን ጨምሮ በ16 ከተሞች ባካሄዱት ጥናት ማረጋገጣቸውን የሚገልጽ ሠነድ ይፋ አድርገዋል፡፡ "ሽብርተኝነት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሥጋት ነው ብለው ያስባሉ?" የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉን በተመለከተ ያልዎት እምነት ምንድን ነው?" መንግስት የፀረ ሽብርተኝነት ህጉን ተቃዋሚዎችን በማፈንና ሰብዓዊ መብትን ለመርገጥ ተጠቅሞበታል? የሚሉና መሠል ጥያያቄዎችን ያካተተው የሁለቱ ድርጅቶች ጥናት እንደሚያመለክተው ሽብርተኝነት እና የሃይማኖት አክራሪነት ለኢትዮጵያ ሥጋት መሆናቸውን ነው፡፡ ስለሆነም ማነው ሽብርተኛ? እና አክራሪ? ለሚለው የከሰሩ ፖለቲከኞች  ጥያቄና ግራ መጋባት ይህ ጥናት ግራ መጋባታቸውን የሚመልሥ ሲሆን  እነዚህ ግለሰቦች ህዝቡ ብለው በጅምላ ህዝብ የመንግስትን አካሄድ አልተቀበለውም ላሉትና የትኛው ህዝብ ስል ለጠየኳቸው ጥያቄ በቂና ግልጽ ምላሽ የሚሠጥ ጥናት ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ስለሆነም በዚህ አጋጣሚ የጥናቱን አንኳር ነጥብና ተያያዥ ጉዳዮች ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ የሠኞ ሐምሌ 22/2005 ዕትምና ከሁለቱም ጥናት አድራጊ ድረ ገጾች መመልከት እንደሚቻል አስታውሼ ወደሌላውና ከአክራሪነት እና ከከሰሩ ፖለቲከኞች ጋብቻ የሚቀፈቀፉ ሽብርተኞችንና መዘዛቸውን ወደተመለከቱ ትርክቶች  ልሸጋገር፡፡

ሽብርተኝነት የተወሰኑ ቡድኖች ወይም ክፍሎች የፖለቲካ አላማቸውን ወይም አመለካከታቸውን በማስፈራራትና ሃይልን በመጠቀም በህዝብ ላይ ለመጫን የሚፈጽሙት ወይም የሚሞክሩት አደገኛና አሠቃቂ የጥፋት ተግባር ነው፡፡

እስከ ዛሬ በተግባር እንደታየው ሽብርተኝነት በህዝብና በመንግስት ላይ ሥጋት የሚያስከትል እንደሆነ ቢታመንም በአብዛኛው የጥቃት ዓላማ አድርጎ የሚንቀሳቀሰው

በሠላማዊ ህዝብ ላይ ነው፡፡ ይሄም በመሆኑ አሸባሪዎች የንጹሃን ሠዎችን ህይወት በማጥፋት ህዝብ መገልገያ ተቋማትን በማውደም ላይ ያተኮረ እጅግ አስከፊ የሆነ ኢ-ሠብአዊ ድርጊት ሲፈጽሙ ተስተውሏል፡፡

ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ የሚካሄዱት ግጭቶች ወይም ግጭት የማነሳሳት ሙከራዎች በተለያየ ደረጃ የሚታይ አሉታዊ ውጤት የሚኖራቸው መሆኑ በተግባር እየታየ ነው፡፡ ግጭቶች በትንሽ በትንሹ ብቻ የሚከሰቱ ከሆነ ምን ጊዜም ቢሆን የስጋት መንፈስ መፍጠራቸውና ተጨባጭ ጉዳት ማስከተላቸው ሳየታለም የጠፈታ ነው፡፡ ታዲያ እነዚህ ትንንሽ የሚመስሉ ነገር ግን ደግሞ በየእለቱ የሚደጋገሙ የግጭት ክስተቶች በህዘብ ላይ ከባድ ስነልቦናዊ ተፅእኖ እያሳረፉ ነው፡፡ አንዱ ግጭት ለሌላ ግጭት መቀስቀስ በር እየከፈተ ነገሩ ሁሉ ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆን ሊያደርጉም ይችላሉ፡፡ በዚሁ ልክ ደግሞ ሰላምና መረጋጋት የጠፋበት አገር መስለን እንድንታይና ገፅታችን እንዲበላሽም እያደረጉ ነው፡፡ ከነዚህ ትንንሽና የማያቋርጡ ግጭቶች ባሻገር በሃይማኖት ሽፋን የሚቀሰቀስ ከፍኛ ግጭት ሲኖር ደግሞ ለበርካታ ህይወት መጥፋት፣ ለከፍተኛ ንብረት ውድመትና በህዝቦች መካከል በቀላሉ የማይበርድና ለቀጣይ ግጭትና ፍጅት በር የሚከፍት የጥፋ አዙሪት ይከፈታል፡፡

በሃይማኖት ሽፋን የሚካሄዱ ግጭት የመቀስቀስ ሙከራዎች ላይ ላዩን ሲታዩ ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው መስለው ይታያሉ፡፡ ይሁንና ጉዳዩን በጥልቀት ለመመልከት ሲሞከር ሃይማኖቶች የግጭት መንስኤ እንደማይሆኑ ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡

ሃይማኖቶች የግጭት መንስኤ አይደሉም፣ ሊሆኑም አይችሉም የሚባልበት ምክንያት ማንኛውም ሃይማኖት በወሳኝነት ፍቅርና ሰላምን፣ ትዕተግስትና መቻቻልን የሚያስተምር እንጅ ጥላቻና ግጭትን የሚሰብክና የሚቀሰቅስ ይዘት ስለሌለው ነው፡፡ የክርስትና እምነት የሚመራበት መፅሃፍ ቅዱስ አንድ ጉንጭህን ሲመታህ ሌላውን ስጥ በማለት የሚገልፀው ትእግስትና መቻቻልን ለማመልከት እንጅ በሰበብ አስባቡ መጋጨትን ለማምጣት አይደለም፡፡ በደል ያልፈፀመን ዜጋና የማንኛውም እምነት ተከታይ ቀርቶ በደል የፈፀመም ቢሆን የበደሉንን ሁሉ ይቅር እንድንል የሚያስተምረው መፅሃፍ መቼም ቢሆን የግጭት መንስኤ ሊሆን አይችልም፡፡ በቁርአንም ቢሆን ተመሳሳይ ነው፡፡ እስልምና የሰላም ሃይማኖት እንደሆነ በመፅሃፉ ተደጋግሞ የተገለፀ ከመሆኑም በላይ ቁርአን መቻቻልንና መከባበርን ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ የእምነት መመሪያ ነው፡፡ ከጊዜ በኋላ በአለማችን

የተከሰቱ ሌሎች ዘመናዊ ሃይማኖቶችም ቢሆኑ ፍቅርንና መከባበርን እንጅ ጥላቻና ግጭትን የማራመድ ይዘት የላቸውም፡፡

ከዚህ በመነሳት ሲታይ ሃይማኖትን በሽፋንነት በመጠቀም የሚካሄዱ ማናቸውም ቅስቀሳ ሆነ የማነሳሳት ሙከራ ሃይማኖታዊ መሰረት እንደሌለው ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሃይማኖትን በሽፋንነት መጠቀሚያ ሆነ እንጅ ዋናው የችግሩ መንስኤ በግጭት እንጠቀማለን ብለው የሚያስቡና የሚንቀሳቀሱ ሰዎች መኖራቸው ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በአገራችን ብቻ ሳይሆን በመላው አለም የሚገኙ ሲሆኑ ፍላጎታቸውን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የበላይ ለማድረግ ሲሳናቸው ሃይማኖትን ሆነ ማናቸውንም ጉዳይ ለግጭት መቀስቀሻ አላማ እንደሚጠቀሙበት የታወቀ ነው፡፡ በመሆኑም በሃይማኖት ሽፋን የሚደረገው ግጭት የመቀስቀስ ሙከራና እንቅስቃሴ መሰረቱ የከሰረ ፖለቲካ እንጂ ሃይማኖት ነው ሊባል አይችልም፡፡ ይህን ለማረጋገጥም ብዙ ሩቅ መሄድ አያስፈልገንም ሰሞንኛዎቹን የሰማያዊ ፓርቲ እና የአንድነት ፓርቲን በሰላማዊ ሰልፍ ስም የተቀነባበሩ ሴራዎች ማስታወስ በቂ ነው።

ህገ መንግስታችን ሃይማኖት የግል እንደሆነና በኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ሃይማኖቶች እኩል እንደሚታዩ በግልፅ ደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት የማንኛውም እምነት ተከታይ ዜጋ ሃይማኖታዊ ደንቡ የሚፍቅደውን የአምልኮ ስርዓት በነፃነት ተግባራዊ እንዲያደርግ፣ ይህን በማድረጉም ከማንም ወገን አንዳች አይነት ተፅእኖ እንዳይደርስበት ጥበቃ ይደረግለታል፡፡ በተጨማሪም ለሃይማኖታዊ አድሎ አንድ መሠረት የነበረውን መንግስታዊ ሃይማኖት እንዲኖር የማድረግ አሰራር ሙሉ በሙሉ በማስወገድ መንግስትና ሃይማኖት እንዲነጣጠሉ አድርጓል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሃይማኖትና ትምህርት፣ ሃይማኖትና ሚዲያ በህግ እንዲለያዩ ተደንግጓል፡፡ እነዚህ ሁሉ ህጋዊ ድንጋጌዎች በተግባር እንዲውሉ በመደረጉ በአገራችን በሃይማኖቶች መካከል ለመበላለጥና በዚህም ምክንያት ሊቀሰቀስ ለሚችል ግጭት አንዳችም ህጋዊና ፖለቲካዊ መሰረት እንዳይኖር ተደርጓል፡፡

ህገ መንግስታችን ለሃይማኖት እኩልነት እንጅ ለአድሎና መበላለጥ ቦታ የለውም፡፡ ባለፉት 22 ዓመታት ሃይማኖታዊ እኩልነቱን በተግባር ለማዋል ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ ለሚካሄድ ግጭት አንዳችም የረባ ህጋዊና ፖለቲካዊ ምክንያት በሌለበት ወቅት የሚካሄዱ ግጭት የመቀስቀስ ሙከራዎች ሁሉ መንስቴያቸው አሁንም ፍላጎታቸውን በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ ማራመድ የተሳናቸው

ወገኞች እንደሆኑ አመላካች ነው፡፡ እነዚህም የሃይማኖት ጉዳይ ለእያንዳንዱ ሰው ልቦና የቀረበና በቀላሉ የሚስማማው እንደሆነ በመገንዘብ እውነታውን አጣመውና ስሜት በሚቀሰቅስ የቅጥፈት መረጃ አውገርግረው በማቅረብ ሲሞክሩ የምንመለከተው ከዚህ በመነሳት ነው፡፡

በአገራችን በመገንባት ላይ ያለውን ህገ መንግስታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለየት የሚያደርገው አንድ ጉዳይ በህገ መንግስታችን ላይ የሰፈሩ መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት የሚደረግ በመሆኑ ነው፡፡ መንግስት ከዚህ አኳያ ሲታይ የህገ መንግስቱን ቃልና መንፈስ በትክክል ስራ ላይ ለማዋል ያልተቆጠበ ጥረት አድርጓል፡፡ የሃይማኖት እኩልነትን በተመለከተ የተደረገው ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ዜጎች ያለማንም አስገዳጅ በመረጡት ሃይማኖት እንዲመሩ፣ ሃይማኖታዊ ግዴታቸውን ያለማንም ጣልቃ ገብነት እንዲወጡ፣ መንግስትና ሃይማኖት እንዲሁም ሃይማኖት ከሚዲያና ከትምህርት በተግባር ተነጣጥለው እንዲቀጥሉ በማድረግ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌውን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ቀደምት ስርአቶች ይከተሉት በነበረው የሃይማኖት ጭቆና መርህ ምክንያት የተፈጠሩና ሥር ሰደው የቆዩ የፍትህ መጓደሎችን በተግባር ለማረምም በጣም ትል ቦታ የሚሰጠው እርምጃ ወስዷል፡፡ የእምነት ቦታዎችን ለመገንባት የነበሩ ችግሮችን በመቅረፉ ባለፉት 22 አመታት በሁሉም ሃይማኖቶች ዘንድ የእምነት መዳረሻ ቦታዎች በከፍተኛ መጠንና ፍጥነት ተስፋፍተዋል፡፡ሃይማኖታዊ በአላት አገራዊ እውቅና ከማግኘት አልፈው በአለም አቀፍ ደረጃ የመቻቻል ባህላችን ማሳያዎች እንዲሆኑም ባደረገ አኳኋን ጭምር በትልቁ እንዲከበሩ ሁኔታው ተመቻችቷል፡፡

ከዚህ በመነሳት ሲታይ ህገ መንግስታችንን በተግባር ለማዋል የተደረገው ጥረት እንደማንኛውም ጀማሪ ዴሞክራሲ ብዙ የሚሻሻሉና የሚዳብሩ ገጽታዎች እንዳሉት የታመነ ሆኖ አገራችን ትክክለኛ አቅጣጫ ይዞ በመጓዝ ላይ መሆኗን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም የሃይማኖት እኩልነት በተግባር ለመተርጎም የተደረገው ጥረት መቻቻልን ይበልጥ የሚያሰፉና የሚያረጋግጥ እንጂ ለግጭት በር የከፈተና የሚከፍት አልነበረም፡፡

እዚህም ላይ ተጨባጭ ሁኔታው ለግጭት መንስኤ የሚሆን ጥፋት የሚታይበት ባልሆነበት ግጭት የመንቀሳቀስ ሙከራው በአክራሪ አስተሳሰብ የተሞሉ ሰዎች የስራ ውጤት እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

የአገር ውስጥ የከሰሩ ፖለቲከኞች እና የኒዮ ሊበራሊስት ሃይሉ ስመ ጋዜጠኛ ቅጥረኞች ሃይማኖትን እንደ ምሽግ መጠቀም መርጠዋል።በአገራችን የሃይማኖት እኩልነት በህግና በተግባር ለማረጋገጥ በተካሄደ ትግል የተሳካ ውጤት ለማምጣት ቢቻልም የከሰሩ ፖለቲከኞች በሃይማኖት ዙሪያ ሁከትና ብጥብጥን ለመቀስቀስ የማይሞክሩት ነገር የለም፡፡ እነዚህ ሃይሎች በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ ሰርገው በመግባት ሃይማኖቱን በፖለቲካ ለመበረዝ የማያደርጉት ጥረት የለም፡፡ በዚህ መሰረት የከሰሩ ፖለቲከኞች የወቅቱ ስልት በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ሰርገው በመግባት ሃይማኖትን የፖለቲካ አላማቸው ማራመጃ ማድረግ ሆኗል፡፡

ሃይማኖትን በሽፋንነት ለመጠቀም የሚሹት እነዚህ ሀይሎች በኦርቶዶክስም ሆነ በእስልምና ሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ቀላል በማይባል ደረጃ ሰርገው ለመግባት ችለዋል፡፡ አንዳንድ የሃይማኖት ተቋማትን የፖለቲካ አላማ ማስፈጸሚያ ለማድረግ ሲረባረቡ የምንመለከተው ከዚህ በመነሳት ነው፡፡ የከሰሩ ፖለቲከኞች በሃይማኖት ተቋማት ዙሪያ ሰርጎ በመግባት በመበከል የሚፈልጉትን የገበያ ግርግር ለመፍጠር ሲንቀሳቀሱ መመልከት የተለመደ የሆነውም ለዚሁ ነው፡፡

የከሰሩ ፖለቲከኞች ሰርገው ለገቡበት ወይም ደግሞ ለብጥብጥ መፍጠሪያ በሽፋንነት ለሚጠቀሙበት ሃይማኖት አክብሮት እንደሌላቸው ለመገንዘብ የተለየ ጥበብ አይጠይቅም፡፡ ሃይማኖትን ለፖለቲካ አላማ ማራመጃ ሽፋን አድርጎ በመጠቀም ሆነ በቀጥታ ይህን በመሳሪያነት ጥቅም ላይ ማዋል ለሃይማኖት ፊፅሞ ደንታ ቢስነትንና ክብር የለሽነትን የሚያሳይ ነው፡፡ ሃይማኖትን የሚያከብር ሰው በሃይማኖት ስም ወንጀል ለመፈፀም ፈፅሞ ሊንቀሳቀስ አይሞክርም፡፡ የአገራችን የከሰሩ ፖለቲከኞች በሃይማኖት ውስጥ መሽገውና ይህንኑ በሽፋንነት እየተጠቀሙ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የመሸጉበትን ሃይማኖቶች የሚያረክስ መሆኑ አይቀርም፡፡

በምገኝበት ወቅት የከሰሩ ፖለቲከኞች ሃይማኖትን መጠጊያና ምሽግ አድርገው እንዲቀሳቀሱ የሚያስገድድ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በዚህ ረገድ ከሚታዩት ነገሮች ቀዳሚው የአገራችን የጥፋት ፖለቲከኞች ባለፉት ጥቂጥ አመታት በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ትግል በከፍተኛ ደረጃ መጋለጣቸውና መሸነፋቸው ነው፡፡ ስልጣንን ከተቻለ በምርጫ ካልተቻለ ደግሞ በሃይል ለመያዝ አልመው የተነሱት ሃይሎች በሁለቱምመንገድ እንደተሸነፉ በግልጽ ይታወቃል፡፡ የአገራችን የከሰሩ ፖለቲከኞች በምርጫ ውድድር የደረሰባቸው ሽንፈትና በይፋ ያካሄዱት የአመፅ ሙከራ ክሽፈት ሲያጋጥማቸው አሁን ደግሞ ሃይማኖቶችን መጠጊያ በማድረግ የሃይማኖት ግጭትን እንደ አንድ የትግል ስልት በመጠቀም ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ሂደት ሃይማኖቱን የሚወድና በእርግጥም ሃይማኖቱ ለአደጋ የተጋለጠ መስሎት የተደናገረ አማኝ ባይታጣም እንቅስቃሴውን የሚመሩና የሚያሰተባብሩት ግን ፅንፈኛ የፖለቲካ ሃይሎች እንደሆኑ የሚያጠያይቅ ነገር አይደለም፡፡

በሃይማኖት ሽፋን ግጭትን ለመቀስቀስ የሚደረገው ሙከራ በዋነኛነት በአገር ውስጥ ባሉ የከሰሩ ፖለቲከኞች፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘ አኳኋን ደግሞ ኢትዮጵያን የአለምአቀፍ የአክራሪዎች ሽኩቻ መናሃሪያ ማድረግ በሚፈልጉ የውጭ ሃይሎች የተጠነሰሰና የሚራመድ ቢሆንም ለዚሁ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር የመንግስት ድክመትም የለም ማለት አይቻልም፡፡ ከነዚህ ድክመቶች አንዱና ትልቁ ከሃይማኖት ተፅእኖ ነፃ መሆን ያለበትን መንግስት የሃይማኖት መሳሪያ ለማድረግ በሚካሄደው ጥረት ሰለባ የሆኑ የመንግስት አካላት መኖር ነው፡፡ አልፎ አልፎ እንደሚታየው በተለያ ደረጃዎች የሚገኙ አንዳንድ የመንግስት ሃላፊዎች በግላዊ እምነታቸውና በመንግስት ሃላፊነታቸው መካከል ልዩነት ማድረግ ሲሳናቸው ይታያል፡፡ ጁነዲን ሳዶን ያስታውሷል ።ለማንም ግልፅ እንደሚሆነው የሃይማኖት ነፃነት በተከበረበት አገር የመንግስት ሰራተኞችንና ሃላፊዎችን ጨምሮ ማንኛውም ሰው በመረጠው ሃይማኖት የመመራት መብት አለው፡፡ ይህንንም ህግና ስርዓቱን ተከትሎ መግለፅ ይቻላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳች አይነት ብዥታ የለም ሊኖርም አይገባውም ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን የመንግስት ሰራተኞችና ሃላፊዎች የመንግስት ስራቸውንና ሃላፊነታቸውን ከሃይማኖታዊ ዝንባሌዎችና ግዴታዎች ነፃ በሆነ አኳኋን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ሃይማኖት መንግስታዊ አገልግሎት ለዜጎችና ለህዝብ ለመስጠት መስፈርት ሆኖ እንዲያገለግል ማድረግ በህግ የተከለከለና የማይገባ ነው፡፡ በመሆኑም የራስን ሃይማኖት የመከተል መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስታዊ አገልግሎት ግን ያላአንዳች

አድሎ ለሁሉም እምነት ተከታይ ዜጎች በእኩልነትነ ማበርከት ህገ መንግስታዊ ግዴታ መሆኑን የተገነዘበ አካሄድ መከተል ያስፈልጋል፡፡

በመካሄድ ላይ ያለው ሃይማኖትን እንደ ሽፋን በመጠቀም ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መነሻና መድረሻው በትርምስ ውስጥ የፖለቲካ ትርፍ ማግኘት ነው፡፡ የፖለቲካ ትርፍ በግርግር መካከል ስልጣን መያዝ ወይም መጋራትን ጨምሮ ይህ የፖለቲካ ሃይል ወደስልጣን ካልመጣ አገሪቱን ማተራመስና በቀላሉ የማትተዳደር እስከማድረግ ሊደርስ ይችላል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ስልጣን በድርድርም ሆነ ህገመንግስታዊ ባልሆነ በማናቸውም መንገድ የማይያዝ በመሆኑ የከሰሩ ፖለቲከኞች በህዝብ ውስጥ ሃይማኖትን ሽፋን ያደረገ ግጭትና ትርምስ በማቀጣጠል ወደስልጣን የሚመጡበት እድል የለም፡፡ እነዚህ ሃይሎች በየቦታው ትንንሽ ወይም መካከለኛ ግጭቶችን በመቀስቀስ በሚያካሂዱት እንቅስቃሴ በህዝብና በአገራችን ላይ በርካታ ጉዳት ማድረስ ግን ይችላሉ፡፡ በተለይ ከራሳቸው አልፈው ህዝቡን አደናግረው ሰፋ ባለ አኳኋዋን የተሳሳተ አላማቸው ማስፈፀሚያ ካደረጉት ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑ አይቀሬ ነው።

በሃይማኖት ሽፋንም ሆነ በሌጣው በሚካሄድ ፖለቲካዊ ማነሳሳት ምክንያት የሚቀሰቀስ ግጭት የመጀመሪያው ትልቅ ጉዳት በህዝብ ህይወትና ንብረት ላይ የሚደርሰው ነው፡፡ ሩቅ ሳንሄድ በ97 ምርጫ ማግስት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስራ አጡንና ተስፋ የቆረጠውን የህብረተሰብ ክፍል በማደናገር አነሳስተው በቀሰቀሱት ግጭት ዜጎች ለእልፈተ ህይወት ተዳርገዋል፡፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወገኖችም ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል፡፡ ይህ ሊቀር የሚችልና የሚገባው የህይወትና የአካል ጉዳት ነበር፡፡ በንብረት ውድመትም ረገድ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል፡፡ ሃይማኖትን ሽፋን ባደረጉ አካባቢያዊ ግጭቶችም ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ልዩ ልዩ ጉዳቶች ደርሰዋል፡፡

ሃይማኖትን ወይም ሌላ ጉዳይን ሰበብ አድርጎ የሚራመድ ግጭት ጥቂትም ይሁን በርካታ ዜጎችን ለእልፈተ ህይወት መዳረጉ አይቀርም፡፡ ንብረትም እንዲወድም ማድረጉ አይቀሬ ነው፡፡ በዚህ ዓይነቱ ግጭት ሁሉ እንደሚታየው የግጭቱ ጠንሳሾች ለጉዳት ብዙም አይጋለጡም፡፡ በከሰሩ የፖለቲካ ሃይሎች ቅስቀሳ ግራ ተጋብቶና የሚያነሱት ሃሳብ የሚያዋጣ መስሎት የሚማገደው ግን ራሱንና ቤተሰቡን ይጎዳል፡፤ ከ97 ምርጫ በኋላ ቅንጅት በቀሰቀሰው ግጭት የተጎዱት በአብዛኛው የፖለቲካ ፍላጎትና አቋም ያልነበራቸው ወገኖች ናቸው፡፡ ከግርግሩ እናተርፋለን ብለው የግጭት አቅጣጫውን የቀየሱና

ያስተባበሩት ግን በኋላ መንግስት በህግ ተጠያቂ አድርጎ ለእስር እስኪዳርጋቸው ድረስ አንዳችም ጉዳት አልደረሰባቸውም፡፡ በህጋዊ ትግሉም ቢሆን ከፖለቲካ ኪሳራ የላቀ ችግር አልደረሰባቸውም፡፡

ለማንም ግልፅ እንደሚሆነው ትልቁ የአገራችን ሃብት ህዝቧ ነው፡፡ ከግለሰብ ዜጎችና ከህዝቧ የሚበልጥ ሌላ ሃብት ለሌላት አገራችን በአንድ ግለሰብ ዜጋ ላይ የሚደርስ ጉዳት ትልቅ ጉዳት ነው፡፡ በግጭት ምክንያት ጉዳቱ ከአንድ ግለሰብ አልፎ በበርካታ ወገኖች ላይ የሚደርስ ከሆነም ጉዳቱ የከፋ ይሆናል፡፡ ህዝብ በሃይማኖት ሽፋት ጎራ ለይቶ የሚጋጭበት ሁኔታ ሲፈጠር በጣት የሚቆጠሩ ብቻ ሳይሆን እጅግ ብዙ ዜጎችና የህብረተሰብ ክፍሎች በቀጥታ የጉዳቱ ሰለባ ይሆናሉ፡፡ በአካል ከተጎዱት በተጨማሪም በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ ከባድ ጦስ ማስከተሉ አይቀርም፡፡ የከሰሩ የአገር ውስጥ ፖለቲከኞች ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ ግጭት ለመቀስቀስ የሚያደርጉትን ሙከራ አምርረን መቃወምና ማክሸፍ የሚኖርብን ሰአት ቢኖር አሁን ነው የምለው ከዚህ በመነሳት ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ኢትዮጵያን የዓለም አቀፍ ሃይማኖታዊ ፍልሚያ አውድማ ለማድረግ በውጭ ሃይሎች የሚካሄደውን ያልቆጠበ ጥረት ማምከኛ ሰአት ላይ ነን አሁን የምለውም በሃይማኖት ሽፋን የሚቀሰቀስ ግጭት ባህር ማዶ ተሻግሮ ዓለምአቀፍ ስፖንሠሮቹን እንደማይነካና በዋነኝነት የሚለበልበው እኛን ኢትዮጵያውያንን እንደሚሆን ስለምገነዘብ ነው፡፡ በሃይማኖት ሽፋን የሚቀሰቀስ ግጭት ጦሱ ከዚህም የከፋና በርከት ያለ ነው።በተከታዩ ክፍል እንመለከታቸዋለን።